**SIDAAMU DAGOOMU QOQQOWI MOOTIMMA AFFINI GAAZEEXA**

**የሲዳማ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት አፍኒ ጋዜጣ**

**SIDAAMA NATIONAL REGIONAL STATE AFFINI GAZETA**

| | | |
|---|---|---|
| 1ki Diro Kiiro 12<br>Hawassa, Badheessa 10, 2013 M.D | Sidaamu Dagoomu Qoqqowi Mootimma Amaalete Mini Allaalshi Hundaanni Fulinoho<br>በሲዳማ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ | ፩ኛ ዓመት ቁጥር ፲፪<br>ሀዋሳ፣ መጋቢት ፲ ቀን ፳፻፲፫ ዓ.ም |



**Amado**

**Wodhote Kiiro 12/2013**

**Sidaamu Dagoomu Qoqqowi Mootimma Bushshu Shiilo Shiqishate, Tuqisatenna Womaashshu Gashshooti Wodho ………………… Qoola ….**

**ማውጫ**

**ደንብ ቁጥር ፲፪/፳፻፲፫**

**የሲዳማ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የአፈር ማዳበሪያ አቅርቦት፣ ስርጭትና ገንዘብ አስተዳደር ደንብ ……………… ገጽ…**


**Wodhote Kiiro 12/2013**

**Sidaamu Dagoomu Qoqqowi Mootimma Bushshu Shiilo Shiqishate, Tuqisatenna Womaashshu Gashshooti Wodho**

Bushshu shiilo shiqonna beehaache yannatenni, fulo ajishannohanna iillasi buunxanni loosu amanyoote diriirsa hasiissinohura,

Qoqqowu mootimma baajeetete wowe ikkiteenna bushshu shiilo hirotenni shiqqe horoonsidhannorira anga baatatenninna liqootenni beenkanniha ikkinohura shiilo amandanninna agarranni gara, hattono hirroonni womaashsha gamba assanna qola mittu seeru biso

**ደንብ ቁጥር ፲፪/፳፻፲፫**

**የሲዳማ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የአፈር ማዳበሪያ አቅርቦት፣ ስርጭትና ገንዘብ አስተዳደር ደንብ**

የአፈር ማዳበሪያ አቅርቦትና ስርጭት ቀልጣፋ፣ ወጪ ቆጣቢና ተደራሽነት የሚያረጋግጥ የአሠራር ሥርዓት መዘርጋት በማስፈለጉ፣

በክልሉ መንግስት የበጀት ዋስትና የአፈር ማዳበሪያ በግዥ ቀርቦ ለተጠቃሚዎች እጅ በእጅ ክፍያ እና በብድር የሚሰራጭ በመሆኑ የማዳበሪያ አያያዝና አጠባበቅ፣ የሽያጭ ገንዘብ አሰባሰብና አመላለስ በአንድ ህጋዊ አካል በባለቤትነትና ተጠያቂነት

afi’rinohu annimmatenninna xa’mama noo garinni loosa hasiissannohura,

Sidaamu Dagoomu Qoqqowi Mootimma Jeefisiisaanote Amaale Mini Qoqqowu Bayriidi Seeri quwa 57(6) hunda uynoonnisi biilloonyi garinni tenne wodho fushshino.

**GAFA MITE**

**<u>Xaphooma Woro</u>**

**1. Harancho Umo**

Tenne Wodho “Sidaamu Dagoomu Qoqqowi Mootimma Bushshu Shiilo shiqisho, Tuqishshinna Womaashshu Gashshooti Wodho kiiro 12/2013” yine woshshinara dandiinanni.

**2. Tiro**

Qaalu horo wole tiro uysiissannoha ikka hoogguro tenne wodho giddo:

1. “**Qoqqowo”** yaa Sidaamu Dagoomu Qoqqowooti;
2. **“Biiro”** yaa Sidaamu Dagoomu Qoqqowi Mootimma Giwirinnu Biirooti;
3. **“Borrote Mine”** yaa Sidaamu Dagoomu Qoqqowi Mootimma Mittimmate Loosi Maamarra tantanonna Halashsho Borro Mineeti;
4. “**Baanke**” yaa qoqqowu mootimma baajeette wowe e’eenna bushshu shiilo hirranni

በሚያሰፍን አግባብ ማከናወን በማስፈለጉ፣

የሲዳማ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት መስተዳድር ምክር ቤት በክልሉ ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፶፯(፮) ላይ በተሰጠው ሥልጣን መስረት ይህንን ደንብ አውጥቷል፡፡

**ክፍል አንድ**

**<u>ጠቅላላ ድንጋጌ</u>**

**1. አጭር ርዕስ**

ይህ ደንብ “የሲዳማ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የአፈር ማዳበሪያ አቅርቦት፣ ስርጭትና የገንዘብ አስተዳደር ደንብ ቁጥር ፲፪/፳፻፲፫” ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

**2. ትርጓሜ**

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ ደንብ ዉስጥ፡-

1. **“ክልል”** ማለት የሲዳማ ብሔራዊ ክልል ነው፤
2. **“ቢሮ”** ማለት የሲዳማ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የግብርና ቢሮ ነው፤
3. **“ጽሕፈት ቤት”** ማለት የሲዳማ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የሕብረት ሥራ ማህበራት ማደራጃና ማስፋፊያ ጽ/ቤት ነው፤
4. **“ባንክ”** ማለት በክልሉ መንግሥት የበጀት ዋስትና ለማዳበሪያ መግዣ የሚሆን ገንዘብ

womaashsha liqiissitanno Itiyophiyu Daddalu Baankeeti;

5. "**Worada**" yaa Sidaamu Dagoomu Qoqqowi Mootimma hunda uurrinsoonni woradu taqaati;

6. "**Quchumu Gashshoote**" yaa kantiibunni massagantanno quchumu tantanooti;

7. "**Ollaa**" yaa baadiyyete woradira woy quchumu gashshooti hundaanni afantanno shiimiidi gashshooti taqaati;

8. "**Suuqotenna Liqoote Mittimmate Loosi Maamara**" yaa miilla uminsa fajjonni uurrisidhino seeru mannimma afi'rino womaashsha suuqi'ne liqii'nanni mittimmate maamaraati;

9. "**Yuneene**" yaa lamunna hakkonni aleenni ikkitino kaimu mittimmate loosi maamarra mitteenni uurrisidhino seeru mannimma noose uurrinshaati;

10. **"Kaimu Mittimmate Loosi Maamara**" yaa miilla uminsa fajjonni uurrisidhino seeru mannimma afi'rino maamaraati;

11. "**Bushshu Shiilo**" yaa mu'rote sagalimmate hasiissanno mineraale amadinoha mannu loosinoricho ikke karsado, akatu karsado, du'namaanchonna qunqumadu widira soorramino bushshu shiilooti;

12. **"Qallo"** yaa e'noonni sheemaati garinni liqoo uytino baankera dirunni woy keeshshitino yanna

አበዳሪ የሆነው የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ነው፤

5. **"ወረዳ"** ማለት በሲዳማ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ስር የተዋቀረ የወረዳ እርከን ነው፤

6. **"ከተማ አስተዳደር"** ማለት በከንቲባ የሚመራ የከተማ መዋቅር ነው፤

7. **"ቀበሌ"** ማለት በገጠር ወረዳ ወይም በከተማ አስተዳደር ስር የሚገኝ ዝቅተኛው የአስተዳደር መዋቅር ነው፤

8. **"የቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማኅበር"** ማለት በአባላት ነጻ ፍላጎት የተቋቋመ የህግ ሰውነት ያለው ገንዘብ እየቆጠቡ የሚበደሩበት ኅብረት ስራ ማህበር ነው፤

9. **"ዩኒየን"** ማለት ሁለትና ከዚያ በላይ በሆኑ መሠረታዊ ኅብረት ሥራ ማኅበራት ኅብረት የተቋቋመ የሕግ ሰውነት ያለው ተቋም ነው፤

10. **"መሰረታዊ ኅብረት ሥራ ማኅበር"** ማለት በአባላት ነጻ ፍላጎት የተቋቋመ የሕግ ሰውነት ያለው ማኅበር ነው፤

11. **"የአፈር ማዳበሪያ"** ማለት ለተክሎች ለምግብነት አስፈላጊ የሆነ ንጥረ-ነገር የያዘ ሰው ሰራሽ ቁስ ሲሆን ድብልቅን፣ አካላዊ ድብልቅን፤ ፈሳሽና ወደ አንኳርነት የተለወጠ የማዳበሪያ ድብልቅን ይጨምራል፤

12. **"ወለድ"** ማለት በውል ስምምነት መሰረት

bikkinni xibbunni shallange baantanni womaashshaati;

13. "**Owaantete Baatooshshe**" yaa yuneene, federeshiinenna kaimu mittimmate loosi maamarra bushshu shiilo amadooshshinna agarooshshi, tuqishshi, hirotenna liqoo qolsiisate aana e'noonni sheemaati garinni uynoonni owaantera shallange baantanni batooshsheeti;

14. "**Amaalate Hedo**" yaa mittu baatto loosi're galinohu loosi'rino baatto bikkinni horonsi'ra hasiissannosi giwaate dananna bikka ogeeyye shallagge uytanno ogimmate hedooti;

15. "**Mancho**" yaa kalaqamu mancho woy seerunni mannimmate qoosso aamantino bisooti.

**3. Koo-teemmate Xawishsha**

Tenne wodho giddo mitte koo-teemmanni worroonnihu horosi garinni wole koo-teemmano hanqafannoho.

**4. Jeefishshu Mami-geeshsha**

Tini wodho qoqqowu gaashshooti danni hundaanni heedhanno woraddanna quchumu gaashshooti giddo heedhe bushshu shiilo horonsidhannori aana jeeffannota ikkitanno.



ለአበዳሪ ባንክ በዓመት ወይም በቆይታ ጊዜ በመቶኛ ተሰልቶ የሚከፈል ገንዘብ ነው፤

13. **"የአገልግሎት ክፍያ"** ማለት ዩኒየኖች፣ ፌደሬሽን እና መሠረታዊ ኅብረት ሥራ ማኅበራት በማዳበሪያ አያያዝና አጠባበቅ፣ ስርጭት፣ ሽያጭና አመላለስ ላይ በውል ስምምነት መሠረት ለሰጡት አገልግሎት ተሰልቶ የሚከፈል ክፍያ ነው፤

14. **"ምክረ-ሀሳብ"** ማለት አንድ አርሶ አደር ባለው ማሳ መጠቀም የሚገባውን የግብአት ዓይነትና መጠን በባለሙያ ተሰልቶ የሚሰጥ ሙያዊ አስተያየት ነው፤

15. **"ሰው"** ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው።

**3. የጾታ አገላለጽ**

በዚህ ደንብ በአንድ ፆታ የተገለጸው እንደ አግባብነቱ ሌላኛውንም ጾታ ያካትታል።

**4. የተፈጻሚነት ወሰን**

ይህ ደንብ በክልሉ አስተዳደር ወሰን ስር በሚገኙ ወረዳዎችና ከተማ አስተዳደሮች ውስጥ በሚኖሩ የአፈር ማዳበሪያ ተጠቃሚዎች ላይ ተፈጻሚ ይሆናል።

## GAFA LAME

**Bushshu Shiilo Shiqisho, Tuqishshinna Womaashshu Gashshooti Amanyoote**

### 5. Bushshu Shiilo Mixo Qixxeessa

1. Deerru deerrunkunni heedhanoti giwirinnu tantano laalchu dirira hasiisannoha bushshu shiilo horonsi’raanote batinyinni, baattote bikkinni, gidu daninni sooreessimmatenni badde deerru deerrunkunni heeranno gashshootu amaale mininni gumulsiissanno.

2. Qoqqowu giwirinnu biiro wonsinoonniha bushshu shiilo bikkunninna danunni, woradahonna, quchumu gashshootira shiqanno base badde mittimmate loosi maamarra tantanonna halashsho borro minera sayissanno.

### 6. Bushshu Shiilo Shiqinshanni Gara

1. Laalchu dirira mixi’nonni bushshu shiilo bikkinna dana kaima assatenni hiratenna tuqisate waaga xiinxallatenni woradahonna quchumu gashshootira qixxeessinanni; Mixo biirote widoonni jeefisiisaanote amaale minira shiqqe gumulantanno.

2. Deerru deerrukunni heerannohu gashshootu amaale mini laalchu dirita bushshu shiilo mixonna liqoote bikka diru hanafora woradu woy quchumu amaale minira shiqishe wonsiisanno.

## ክፍል ሁለት

**የአፈር ማዳበሪያ አቅርቦት፣ ስርጭትና የገንዘብ አስተዳደር ሥርዓት**

### 5. የአፈር ማዳበሪያ ዕቅድ ስለማዘጋጀት

1. በየደረጃው የሚገኝ የግብርና መዋቅር በምርት ዘመኑ የሚያስፈልገውን የአፈር ማዳበሪያ በተጠቃሚ ብዛት፣ በመሬት መጠን፣ በሰብል ዓይነት በኃላፊነት በመለየት በየደረጃው በሚገኝ የአስተዳደር ምክር ቤት ያስወስናል፡፡

2. የክልል ግብርና ቢሮ የፀደቀዉን የዘመኑን የአፈር ማዳበሪያ በመጠንና በዓይነት፣ በወረዳ እና በከተማ አስተዳደር በሚቀርበው ጣቢያ ለይቶ ለሕብረት ሥራ ማህበራት ማደራጃና ማስፋፊያ ጽ/ቤት ያስተላልፋል፡፡

### 6. የአፈር ማዳበሪያ አቅርቦት አሰራር

1. ለምርት ዘመን የታቀደው የአፈር ማዳበሪያ መጠንና ዓይነት ላይ በመመስረት የግዢና ስርጭት ዋጋ በማጥናት በወረዳና በከተማ አስተዳደር ይዘጋጃል፤ ዕቅዱ በቢሮው አማካይነት ለመስተዳድር ምክር ቤት ቀርቦ ይወሰናል፡፡

2. በየደረጃው የሚገኝ የአስተዳደር ምክር ቤት የምርት ዘመኑን የማዳበሪያ ዕቅድና የብድር መጠን በዓመቱ መጀመሪያ ለወረዳ ወይም ከተማ ምክር ቤት አቅርቦ ያፀድቃል፡፡

3. Konni quwi cinaanchu quwi 2 garinni wonsinoonnihu bushshu shiilo hirranni womaashshi liqoo bajeettete wowenni jeefinsanni gede Qoqqowu Amaale Minira shiqqenna wonsinannita ikkitanno.

4. Deerru deerrunkunni heerannohu gashshootu amaale mini konni quwi cinaanchu quwi 2 garinni wonsinoonni bushshu shiilo hirate ikkitanno liqoo bajeettete wowe sumuumme Qoqqowu Faynaansete Biirora uytanno.

5. Qoqowu Jeefisiisaanote Amaale Mini widoonni liqoote xa'mo liqiissitanno baankeranna bajeettete wowe Federaalete Faynaansete Ministerera shiqqanno.

6. Qoqowu Jeefisiisaanote Amaale Mininni riqiwo uynoonninsa bissa konni quwi cinaanchu quwi 5 garinni fajjinoonni liqoora liqiissitanno baanke ledo liqoote sheemaate e'anno.

7. Laalchu dirira qoqqowoho hasiisanno bushshu shiilo Federaalete Giwirinnu Minisitere ledo hasaawatenni gobbaydinni woy gobbate giddonni hirotenni shiqishshanno bissara jeefisiisaanote amaale mininni lekkishsha uyinonni bissa lekkishsha uytanno; liqiissitanno baanke ledono sassoote sheemaate eanoha ikkanno.

8. Gobbate gobbaydinni woy gobbate giddonni hirre shiqinshanni bushshu shiilo haadhe tuqishshu xaawira iillishate looso annimmatenni

3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፪ መሰረት የጸደቀ የማዳበሪያ መግዣ የገንዘብ ብድር በበጀት ዋስትና እንዲፈጸም ለክልል ምክር ቤት ቀርቦ እንዲጸድቅ ይደረጋል፡፡

4. በየደረጃው የሚገኝ አስተዳደር ምክር ቤት በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፪ መሰረት ለጸደቀ የማዳበሪያ መጠን መግዣ የሚሆን ብድር የበጀት ዋስትና ስምምነት ለክልሉ ፋይናንስ ቢሮ ይሰጣሉ፡፡

5. በክልል መስተዳድር ምክር ቤት በኩል የብድር ጥያቄ ለአበዳሪው ባንክ እና የበጀት ዋስትና ለገንዘብ ሚኒስቴር ይቀርባል፡፡

6. በክልል መስተዳድር ምክር ቤት ውክልና የተሰጣቸው አካላት በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፭ መሠረት ለተፈቀደ ብድር ከአበዳሪ ባንኩ ጋር የብድር ውል ስምምነት ይፈጽማሉ፡፡

7. በምርት ዘመኑ ለክልሉ የሚያስፈልግ የአፈር ማዳበሪያን ከፌደራል ግብርና ሚኒስቴር ጋር በመወያየት ከውጭ ወይም ከሀገር ውስጥ በግዢ ለሚያቀርብ አካል በመስተዳድር ምክር ቤት ውክልና የተሰጣቸው አካላት ውክልና ይሰጣሉ፤ ከአበዳሪ ባንኩ ጋርም የሦስትዮሽ ውል ይፈፀማሉ፡፡

8. ከውጭ ወይም ከሀገር ውስጥ ተገዝቶ የሚቀርብ ማዳበሪያ ተረክቦ ለስርጭት ጣቢያ የማጓጓዙን ሥራ በኃላፊነት ለሚሠሩ የኅብረት ሥራ ማኅበራት ወይም ዩኒየኖች በወረዳ ወይም በከተማ አስተዳደር

loossanno mittimmate loosi maamarrara woy yuneennara woradu woy quchumu gashshooti lekkishsha aano gede borrote mini widoonni assinanni; lamenti bissa sheemate e'anno.

9. Woradu woy quchumu gashshooti lekkishshi garinni sheemaate eino kaimu mittimmate loosi maamarra bushshu shiilo haadhe tuqissanno gede assinanni.

10. Mereershu kuusote mininni tuqisate xaawira iillishshanno hodhishshu uurrinshubba mootimmate hirote seeri garinni mitimmate loosi maamarra beeqqo heewisiisatenni doorantanno; sheemaate e'nanni; bobbahishshu hajajo uynanni.

11. Gobbate gobbaydinni woy gobbate giddonni lekkishsha uynoonni bissanni hirotenni shiqqanno bushshu shiilo qoqqowu mereershu kuusote minnara lekkinsonni mittimmate loosi maamarra woy yuneenna haadhanno; bandoonni tuqishshu xaawubbara hodhisanno.

**7. Bushshu Shiilo Waagi Shallagonna Tuqishshu Gara**

1. Bushshu shiilo hirranni waga shallangannihu bushshu shiilo hidhinoonni waaga, gobbate giddo hodhishsha, baankete qallonna inshuraanse, owaantete baatooshshenna tenne hajo ledo xaaddanno fulo shallagatenni mittu mittunku hiranni xaawinni ikkanno.

2. Bushshu shiilo baatto loosidhe galtinorira woy

ውክልና እንዲሰጥ በጽሕፈት ቤቱ በኩል ይደረጋል፤ የሁለትዮሽ የውል ስምምነት ይፈፀማል፡፡

9. በወረዳ ወይም በከተማ አስተዳደር ውክልና መሠረት የሁለትዮሽ ውል ስምምነት የፈጸሙ መሠረታዊ ኅብረት ሥራ ማኅበራት ማዳበሪያ ተረክበው እንዲያሰራጩ ይደረጋል፡፡

10. ከማዕከላዊ መጋዘን ወደ ስርጭት ጣቢያ የሚያጓጉዙ የትራንስፖርት ድርጅቶች በመንግሥት የግዢ ሕግ መሠረት በኅብረት ሥራ ማኅበራት ተሳትፎ በውድድር ይመረጣሉ፤ ውል ይገባል፤ የስምሪት ትዕዛዝ ይሰጣል፡፡

11. ከውጭ አገር ወይም ከሀገር ውስጥ ውክልና በተሰጠው አካል በግዢ የሚቀርብ ማዳበሪያ በክልሉ ማዕከላዊ መጋዘኖች የተወከሉ የኅብረት ሥራ ማኅበራት ወይም ዩኒየኖች ይረከባሉ፤ ለተለዩ የስርጭት ጣቢያዎች ያጓጉዛሉ፡፡

**7. የአፈር ማዳበሪያ ዋጋ ስሌትና የስርጭት አሰራር**

1. የአፈር ማዳበሪያ የመሸጫ ዋጋ የሚሰላው የማዳበሪያ መግዣ ዋጋ፣ የአገር ውስጥ የትራንስፖርት፣ የባንክ ወለድና ኢንሹራንስ፣ የአገልግሎት ክፍያና ተዛማጅ ወጪዎችን በማስላት በያንዳንዱ የሽያጭ ጣቢያ ይሆናል፡፡

2. የአፈር ማዳበሪያ ለአርሶ አደሩ ወይም

horonsi'rannohura tuqinsannihu aante no hirote doorshuwanni ikkanno:

a) Bushshu shillo anga baatte hidhitannorira amaalete hedo garinni noonsa baatto bikkinninna wixidhanno sirchi daninni shallange hasiisannonsaha bushshu shiilo wo'ma baatooshshe baatte adhitanno gede assinanni;

b) Bushshu shiilo anga baatte hidhate wolqa ajjannonsa baatto loosidhe galtinorira miilla ikkitino mittimmate loosi maamariwiinni woy wolootu maykiro faynansete buenni woxe liqiidhe bushshu shiilo hidha dandiitanno; Mittimmate loosi maamari woy wolootu liqiissitanno bissara liqoote baatooshshe liqiissihunna liqii'rihu sumuu yitanno garrinni qallo shallange baantanniha ikkanno.

3. Bushshu shiilo anga baatatenni hirre woxe gamba assinannihu Sidaamu Elto Mittimmate Loosi Yuneene hunda heedhanno kaimu mittimmate loosi maamarranni tenne hajora yine qixxeessinoonni darrasanyinninna uminsa ogeeyyenni calla ikkanno.

4. Bushshu shiilo anga baatatenni hirrannihu mittimmate loosi maamarinni tenne hajora yine qixxeessinoonni darrasanyinni calla ikkeenna borreessinoonni womaashshi bikkinni shiqannoha bushshu shiilo kaimu mittimmate loosu maamari kuusote mininni fulo asse

ለተጠቃሚ የሚሰራጨው በሚከተሉት የሽያጭ አማራጮች ይሆናል:-

ሀ) የአፈር ማዳበሪያ እጅ በእጅ ሽያጭ ለሚገዙት በምክረ-ሀሳቡ መሠረት በማሳቸው መጠንና በሰብሉ ዓይነት ተሰልቶ የሚያስፈልጋቸውን ማዳበሪያ ሙሉ ክፍያ በመፈፀም እንዲወስዱ ይደረጋል፤

ለ) የአፈር ማዳበሪያ እጅ በእጅ ግዢ ለመፈፀም አቅም የሚያንሳቸው አርሶ አደሮች አባል ከሆኑበት ኅብረት ስራ ማህበር ወይም ከሌሎች ማይክሮ ፋይናንስ ምንጮች ገንዘብ በመበደር አፈር ማዳበሪያ መግዛት ይችላሉ፤ ለኅብረት ስራ ማህበሩ ወይም ለሌሎች አበዳሪ አካላት የገንዘብ ብድር ክፍያ ተበዳርውና አበዳሪው አካል በምስማሙት ወለድ መጠን ተሰልቶ የሚከፈል ይሆናል፡፡

3. የአፈር ማዳበሪያ የእጅ በእጅ ሽያጭ ገንዘብ የሚሰበሰበው በሲዳማ ኤልቶ ኅብረት ስራ ዩኒየን ስር በሚገኙ መሰረታዊ ኅብረት ስራ ማኅበራት ለዚሁ ተግባር በታተመ ህጋዊ ደረሰኝና በራሱ ባለሙያዎች ብቻ ይሆናል፡፡

4. የአፈር ማዳበሪያ እጅ በእጅ ሽያጭ የሚከናወነው በኅብረት ስራ ማኅበሩ ለዚሁ ተግባር ተብሎ በተዘጋጀው ደረሰኝ ብቻ ሆኖ በተጻፈበት ገንዘብ ልክ የሚመጣጠን ማዳበሪያ ከመሠረታዊ ኅብረት ሥራ

adhanno.

5. Mittimmate loosi maawarinni tuqinsoonni bushshu shiilo womaashsha sheemaatu garinni barru barrunkunni gamba assine baanke eo assinanni; Qola hoongiro e'noonni sheemaati garinni seeru doogonni qolsiinsanniti noo gedeenni heedheenna baankete qallono lendeenna mittimmate loosi maawari shallagonni baatamanno gede assinanni.

**8. Bushshu Shiilo Horonsi'ranno woy Hidhannohu Qoosso**

1. Ayno bushshu shiilo horonsi'rannohu baatino womaashshira tenne hajora yine qixxeessinoonni darrasanya uyinannisi.
2. Bushshu shiilo baatooshshe baatihunni kayse bati'ranni bati'reenna lamu barri giddo bushshu shiilo afi'ranno.
3. Bushshu shiilota woy hirote waaganna taje afi'rate qoosso noosi.

**GAFA SASE**

**<u>Jeefisiisaano Bissa Biilloonyenna Loosu Qeecha</u>**

**9. Deerru Deerrunkunni Heeranno Dagate Amaale Mini**

1. Laalchu dirita bushshu shiilo mixonna baankete liqoo bikka wonsanno.

ማኅበራት መጋዘን ወጪ አድርጎ ይወስዳል፡፡

5. በኅብረት ስራ ማኅበሩ የተሰራጨ የማዳበሪያ ገንዘብ በውሉ መሠረት በየዕለቱ ተሰብስቦ ለባንክ ገቢ ይደረጋል፤ ካልተመለሰ በውል ስምምነቱ መሰረት በህግ አግባብ የማስመለሱ ተግባር እንደተጠበቀ ሆኖ የባንክ ወለድን በማካተት ከህብረት ስራ ማህበሩ ሂሳብ እንዲከፈል ይደረጋል፡፡

**8. የማዳበሪያ ተጠቃሚ ወይም ገዢ መብት**

1. ማንኛውም የማዳበሪያ ተጠቃሚ ለከፈለው ገንዘብ ለዚሁ ተግባር የተዘጋጀ ደረሰኝ ይሰጠዋል፡፡
2. የአፈር ማዳበሪያ ክፍያውን በፈጸመ ቢበዛ በሁለት ቀናት ውስጥ ማዳበሪያውን ያገኛል፡፡
3. ስለማዳበሪያው ወይም ሽያጭ ዋጋና መረጃዎችን የማግኘት መብት አለው፡፡

**ክፍል ሦስት**

**<u>የአስፈጻሚ አካላት ተግባርና ኃላፊነት</u>**

**9. በየደረጃው የሚገኝ የሕዝብ ምክር ቤት**

1. የምርት ዘመኑን የማዳበሪያ ዕቅድና የባንክ የብድር መጠን ያጸድቃል፡፡

2. Bushshu shiilota baankete liqoo qolate ha’rinsho keenanno, irko assanno.

**10. Deerru Deerrunkunni Heeranno Gashshootu Amaale Mini**

1. Laalchu dirita bushshu shiilo mixonna baankete liqoo bikka gumulanno.
2. Bushshu Shiilo hiroranna labbanno fulora hossanno baankete liqoo bajeettetenni wowe aanno.
3. Bushshu shiilo horonsi’ratenna baankete liqoo qolanni gara ha’runsanno, keenanno.

**11. Olluu Deerri Heedhanno Tantano Biilloonyenna Loosu Qeecha**

1. Olluu giwirinnu borro mini sorreessi woy lekkisaanchi baatto loosidhe galitino ho’ronsiraano su’mi tittirsha, bushshu shiilo bikkanna dana badatenninna qineessatenni gumulosi mittimmate loosi maamarira wixu yannanni ajanni ajeenna mittu agani albaanni saysanno.
2. Olluunnihu loosu qineessaanchi, ollaaho kaimu mittimmate loosi maamari hoogiro maamaru loosonna biilloonye adhe loosanno.
3. Olluunnihu mittimmate loosi maamarra qineessaanchu ogeessi barru barrunniha woxe gamba assate ha’rinshonna woxu tenne hajora fannoonni qoqqowu bushshu shiilo akkawunte kiirora calla easi qorqoratenninna rippoorte

2. የአፈር ማዳበሪያ የባንክ ብድር አመላለስ ይገመግማል፣ ድጋፍ ያደርጋል፡፡

**10. በየደረጃው የሚገኝ የአስተዳደር ምክር ቤት**

1. የምርት ዘመኑን የማዳበሪያ ዕቅድና የባንክ የብድር መጠን ይወስናል፡፡
2. ለማዳበሪያ ግዢና ተዛማጅ ወጪዎች የሚውል የባንክ ብድር በበጀት ዋስትና ይሰጣል፡፡
3. የማዳበሪያ አጠቃቀሙንና የባንክ ብድር አመላለሱን ይከታተላል፣ ይገመግማል፡፡

**11. በቀበሌ ደረጃ የሚገኝ መዋቅር ተግባርና ኃላፊ**

1. የቀበሌ ግብርና ጽ/ቤት ኃላፊ ወይም ተወካይ የተጠቃሚ አርሶ አደር ዝርዝር፣ የማዳበሪያ መጠንና ዓይነት፣ በመለየትና በማደራጀት ውሳኔውን ለህብረት ስራ ማኅበሩ ከዘር ጊዜ ቢያንስ ከአንድ ወር በፊት ያስተላልፋል::
2. የቀበሌ ስራ አስኪያጅ በቀበሌው መሠረታዊ ኅብረት ሥራ ማኅበር ከሌለ የማኅበሩን ተግባርና ኃላፊነት ይወጣል::
3. የቀበሌ ኅብረት ስራ ማኅበራት አደራጅ ባለሙያ የየእለቱን ገንዘብ አሰባሰብና ገንዘቡ ለዚሁ ተግባር በተከፈተው የክልሉ አፈር ማዳበሪያ አካዉንት ብቻ መግባቱን በመቆጣጠርና ሪፖርቱን በማጠናቀር በየሶስት ቀን ለወረዳ ወይም ለከተማ ኅብረት ስራ ጽ/ቤት ሪፖርት ያደርጋል፤ ችግር ስያጋጥም ከወረዳ ኅብረት ስራ

qixxeessanni sasu sasu barrinni woradu woy quchumu mittimmate loosi borro minira rippoorte assanno; Qarru xaadiro woradu mittimmate loosi borro mini ledo halamatenni taashshinanni gede assanno.

**12. Deerru Deerrunkunni Heedhanno Giwirinnu Biiro Tantano**

1. Diroho hasiisanno bushshu shiilo bikka danunni bade mixo qixxeessitanno.
2. Giwirinnu tekinolooje hassattonna loosoho hosase masagganno.
3. Bushshu shiilo shiqonna horonsi'rate gara ha'runsitanno, ragimaletenni woy xaphooma mixonni 15% aleenni galannohunna ajannohu bushshu shiilo heedhuro xa'mantanno.
4. Gobbaanni woy gobbate giddo assinanni bushshu shiilo hirora lekkishsha uytanno; ha'runsitanno; qorqortanno.
5. Bushshu Shiilo silanchimma qorqortanno; amadooshshenna taraawo ha'runsitanno.
6. Bushshu shiilo liqoo qollanni gara ha'runsitanno; hasiisiha ikkiro buuxanno biso gaantara dandiitanno.
7. Jeefisaanonna hajo la'annonsa bissa xaadissanno; qineessitanno; irkissanno.
8. Bushshu shiilo hiro lainohunni mittimmate maamari woy yuneene ledo hirote garanna woxe

ጽ/ቤት ጋር በመሆን እርምት እንድወሰድ ያደርጋል፡፡

**12. በየደረጃው የሚገኝ የግብርና ቢሮ መዋቅር**

1. በዓመቱ የሚያስፈልግ የማዳበሪያ መጠን በዓይነት ለይቶ ያቅዳል፡፡
2. የግብርና ቴክኖሎጂ ፍላጎትና ስርጸት ይመራል፡፡
3. የማዳበሪያ አቅርቦትና አጠቃቀም ይከታተላል፣ ያለአግባብ ወይም ከጠቅላላ ዕቅድ 15 ከመቶ በላይ የሚያድርና የሚያንስ ማዳበሪያ ካለ ኃላፊነት ይወስዳል፡፡
4. በውጭ አገር ወይም በአገር ውስጥ ለሚፈፀም የማዳበሪያ ግዢ ውክልና ይሰጣል፤ ይከታተላል፤ ይቆጣጠራል፡፡
5. የማዳበሪያ ጥራት ይቆጣጠራል፤ አያያዝና ዝውውርን ይከታተል፡፡
6. የአፈር ማዳበሪያ ብድር አመላለስን ይከታተላል፤እንደአስፈላጊነቱ የሚያጣራ አካል ሊመደብ ይችላል፡፡
7. ፈጻሚና የባለድርሻ አካላትን ያስተባብራል፤ ያቀናጃል፤ ይደግፋል፡፡
8. የአፈር ማዳበሪያ ሽያጭ በተመለከተ ከኅብረት ስራ ማኅበር ወይም ከዩኒየን ጋር ስለሽያጭና ስለገንዘብ አመላለስ ውል ይፈፅማል፡፡

qollanni gari sheemaate e’anno.

**13. Deerru Deerrunukunni Heedhanno Mittimmate Loosi Maamarra Tantanonna Halashsho Borro Mini Tantano**

1. Shiqqino bushshu shiilo hassatto taje kaiminni liqoote xa’mo qixxeessanno, jeefisiisaanote amaale mine gumulsiisanno.
2. Liqiissitanno Ityophiyu daddalu baankenni fajjinoonni liqoo horoonsi’ranna qolsiisaa lainohunni womaashshu biiro ledo ikkite sassoote sheemaate eanno; jeefisiisanno.
3. Bushshu shiilo haadhe tuqissannori yuuneenetenna kaimu mittimmate loosi maamarraati.
4. Mittimmate loosi maamarrara bushshu shiilo shiqonna tuqishsha, womaashshu suuqonna liqoo, shallagote amadooshshenna womaashshu gashshooti dhuka kaajjishate looso loosanno.
5. Wodebetenni shiqanno bushshu shiilo dirrinsanni mereerima kuusote minnanna tuqishshu baycho badatenni qixaawanno gede assanno.
6. Mereerima kuusote minnanni tuqishshu xaawira bushshu shiilo iillishate, hodhishshaho ga’rafo fushshanno; mittimmate loosi maamarra ga’rafo fushshitanno gede lekkishsha aanno; tuqishsha massaganno, harunsanno.
7. Assinanni simimme kaiminni hirotenna batooshshu waaxo, mittimmate loosi maamarita

**13. በየደረጃው የሚገኝ ኅብረት ሥራ ማህበራት ማደራጃና ማስፋፊያ ጽ/ቤት መዋቅር**

1. በቀረበ የአፈር ማዳበሪያ ፍላጎት መረጃ መሰረት የብድር ጥያቄ ያዘጋጃል፣ በመስተዳድር ምክር ቤት ያስወስናል፡፡
2. ከአበዳሪ የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ በተፈቀደው ብድር አጠቃቀምና አመላለስን በተመለከተ ከፋይናንስ ቢሮ ጋር በመሆን የሦስትዮሽ ውል ይፈጽማል፣ ያስፈጽማል፡፡
3. የአፈር ማዳበሪያ ተረክቦ የሚያሰራጭ ዩኒየንና መሰረታዊ ህብረት ስራ ማህበር ነው፡፡
4. ለህብረት ስራ ማህበራት ስለ አፈር ማዳበሪያ አቅርቦት ስርጭት፣ ስለ ገንዘብ ቁጠባና ብድር፣ ስለ ሂሳብ አያያዝና ገንዘብ አስተዳደር የአቅም ግንባታ ሥራ ይሰራል፡፡
5. ከወደብ የሚቀርብ ማዳበሪያ የሚራገፍባቸው ማዕከላዊ መጋዘኖችና የማሰራጫ ጣቢያዎች በመለየት እንዲዘጋጁ ያደርጋል፡፡
6. ከማዕከላዊ መጋዘን ወደማሰራጫ ጣቢያዎች ማዳበሪያ ለማጓጓዝ የትራንስፖርት ጨረታ ያወጣል ወይም ለህብረት ስራ ማህበራት ጨረታውን እንዲያወጡ ውክልና ይሰጣል፤ ስርጭት ይመራል፣ ይከታተላል፡፡
7. በሚደረግ ስምምነት መሰረት የግዢና ክፍያ ሚዛን፣ የህብረት ስራ ማህበሩ የማዳበሪያ

bushshu shiilo hironna baankete liqoo qolonna mittimmate loosi maamarrata bushshu shiilo eonna tuqishshu waaxo, qoqqowoho, woraddate yanna yannatenni inspekishiinenna dirunni odiite assanno; deerru deerrunukunni heedhanno gashshootu amaale minira gumulote hedo shiqishanno.

8. Bushshu shiilo hirranni waaganna owaantete baatooshshe gumulitanno, hajo la’annonsa bissara egensiisann.

9. Laalchu dirira bushshu shiilo asale eo assinanni baankete akkawunte fa’nantanno gede assanno; mittimmate loosi maamarraranna hajo la’annonsa bissara egensiisa; baanakete taje harunsanno ogeessa lekkisanno.

10. Bushshu shiilo hirora, gobbate giddo hodhishshira, owaantetenna woloota labbanno baatooshshubba baata woy baatooshshe baantanni gede Itiyophiyu daddalu baankera baatooshshu sanade buuxe saysanno.

11. Bushshu shiilo hironna gobbate giddo hodhishshi baatooshshe bushshu shiilo shiqishshanno uurrinsha woy giwirinnu loossa korporeshiine shiqishate sheemaate e’e shiqisha hanaffuro xaphoomu baatooshshinni 50% balaxote baatooshshe jeefisa, gatinoha bushshu shiilo shiqishe gudiha ikkiro haadhanno mittimmate loosi yuuneenenni shiqishanno seeru taje kaiminni baatanno.

ሽያጭና የባንክ ብድር አመለለስና፣ የህብረት ሥራ ማህበራትን የማዳበሪያ ገቢና ስርጭት ሚዛን በክልል፣ በወረዳ በየወቅቱ ኢንስፔክሽንና በየዓመቱ ኦዲት ያደርጋል፤ በየደረጃው ለሚገኝ የአስተዳደር ምክ ቤት የውሳኔ ሀሳብ ያቀርባል።

8. የማዳበሪያ መሸጫ ዋጋ እና የአገልግሎት ክፍያዎችን ይወሰናል፣ ለሚመለከታቸው አካላት ያሳውቃል።

9. በየምርት ዘመኑ የማዳበሪያ ዕዳ ማስገቢያ የባንክ አካውንት እንዲከፈት ያደርጋል፣ ለህብረት ስራ ማህበራትና ለሚመለከታቸው አካላት ያሳውቃል፣ የባንክ መረጃ የሚከታተል ባለሙያ ይወክላል።

10. ለማዳበሪያ ግዢ፣ የአገር ውስጥ ማጓጓዣ፣ የአገልግሎትና ሌሎች ተዛማጅ ክፍያዎችን መፈፀም ወይም ክፍያ እንድከፈል ለኢትዮጵያ ንግድ ባንክ የክፍያ ሰነድ አረጋግጦ ያስተላልፋል።

11. የማዳበሪያ ግዢና የአገር ውስጥ ማጓጓዣ ክፍያ የአፈር ማዳበሪያ አቅራቢ ድርጅት ወይም ግብርና ስራዎች ኮርፖሬሽን የአቅርቦት ውል ገብቶ ማቅረብ ሲጀምር የጠቅላላ ክፍያ 50 ከመቶ ቅድመ-ክፍያ መፈጸም፤ ቀሪዉን የአፈር ማዳበሪያ አቅርቦ ስያጠናቅቅ ከተረካቢ ህብረት ስራ ዩኒየን በሚያቀርበው ህጋዊ መረጃ መሰረት ይከፍላል።

12. Bushshu shiilo haa'nanninna beenkanni derrasanyuwa attamsiisanno.

13. Suuqotenna liqoote mittimmate loosi maamarra nooikkiwa qoqqowu qooxeessira tantanatanno gede assanno; harunsanno.

**14. Deerru Deerrunkunni Heedhanno Faynaansete Biiro Tantano**

1. Diroho bushshu shiiloranna dooramino wixa hiratenna fiixoontanno fulora hasiissanno liqoo fajjinanni woyte liqqo uyittanno baanke ledo sassoote sheemaate e'anno.

2. Hasiisiha ikkiro diru dirunkunni bushshu shiilo shiqonna tuqishshi hattono faynaansete amanyooti odiite assitanno.

3. Bushshu shiilo eonna fulote sanadda attamisiissanno; tuqissanno.

**15. Mittimmate Loosi Maamarinna Yuneene**

1. Qoqqowu woradu woy quchumi gashshooti riqiwo kaiminni bushshu shiilo haa'ratenna hodhisate mittimmate loosi maamarra tantanonna halashsho borro mini ledo sheemaate e'anno.

2. Mereersanno baycho deerrase agadhitino bushshu shiilo kuunsanni mine qixxeessa, haa'ranna tuqishshu xaawubbara iillishanno.

3. Mittimmate loosi maamarra tantanonna halashsho borro mini woy lekkishsha uynoonnisihu fushshanno hodhishshu ga'rafo

12. ማዳበሪያ መረከቢያና ማሰራጫ ደረሰኞችን ያሳትማል፡፡

**14.** የቁጠባና ብድር ህብረት ስራ ማህበራት በሌሉበት በክልሉ አካባቢዎች እንዲደራጁ ያደርጋል፤ ይከታተላል፡፡

**13. በየደረጃው የሚገኝ የፋይናንስና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ መዋቅር**

1. በዓመቱ ለአፈር ማዳበሪያና ለምርጥ ዘር ግዢና ተዛማጅ ወጪዎች የሚያስፈልግ ብድር ሲፈቀድ ከአበዳሪው ባንክ ጋር የሦስትዮሽ ውል ይፈጽማል፡፡

2. እንደአስፈላጊነቱ በየዓመቱ የማዳበሪያ አቅርቦትና ስርጭት እንዲሁም የፋይናንስ ስርዓቱን ኦዲት ያደርጋል፡፡

3. የማዳበሪያ ገቢና ወጪ ሰነዶችን ያሳትማል፣ ያሰራጫል፡፡

**15. የኅብረት ሥራ ማህበር እና ዩኒየን**

1. በክልል በወረዳ ውክልና መሠረት የአፈር ማዳበሪያ ለመረከብና ለማጓጓዝ ከሕብረት ሥራ ማህበራት ማደራጃና ማስፋፊያ ጽ/ቤት ጋር ውል ይገባል፡፡

2. በማዕከላዊ ቦታዎች ደረጃውን የጠበቀ የማዳበሪያ መጋዘን ማዘጋጀት፣ መረከብ፣ ወደ ስርጭት ጣቢያዎች ያጓጉዛል፡፡

3. የሕብረት ሥራ ማህበራት ማደራጃና ማስፋፊያ ጽ/ቤት ወይም ዉክልና የተሰጠው አካል በሚያወጣው

beeqqanno; qeeltino hodhishshu uurrinsha ledo sheemaate eatenni bobbaysanno.

4. Bushshu shiilo kaimu mittimmate lossi maamarra seerunni attammoonni sanadenni adhitanno gede assatenni uynoonni hodhishshu owaanteranna fiixoontanno fulo sheemaatu garinni baatooshshe haa'ranno; jeefisanno.
5. Gobbate gobbaydinni eino woy haadhe hirote baycho hogonboonni bushshu shiilo taashshatenni xaawunni, woradunna quchumu gashshooti qineesse mittimmate loosi maamarra tantanonna halashsho borro minira liqoote harunso kifilera lamalatenni ripoorte shiqishanno.
6. Lalchu diri goofimarchira qoqqowu mittimmate loosi maamarra tantanonna halashsho borro mini ledo halamatenni magaazinete odiite assiissanno.
7. Horoonsi'raano baattanno womaashshira konni loosira qixxeessinoonni darrasanya qixxeessa.
8. Bushshu shiilo hiratenna womaashsha baanke yannatenni eo assate sheemaate giwirinnu biiro ledo e'anno.
9. Bushshu shiilo hirre gamba assinoonni womaashsha owaantete baatooshshe aaninni xeinse sasu barri giddo dirunnitera bushshu shiilo asale eo assinanni baankete shallago kiirora/account eo assatenni baankete isilipe koppe woradu mittimmate loosi latishshi borro minira shiqishanno.

የትራንስፖርት ጨረታ ይሳተፋል፣ ከአሸናፊው የትራንስፖርት ድርጅት ጋር ውል በመዋዋል ስምሪት ይሰጣል፡፡

4. የአፈር ማዳበሪያውን ለመሠረታዊ ኅብረት ሥራ ማህበራት በታተመ ህጋዊ ሰነድ እንዲረከቡ በማድረግ ለተሰጠ የትራንስፖርት አገልግሎትና ተዛማጅ ወጪዎች በውል ስምምነት ታሪፍ መሠረት ክፍያ ይቀበላል፣ ይፈጽማል፡፡
5. ከውጭ አገር የገባ ወይም የተረከቡትን፣ ወደ ሽያጭ ጣቢያ የተጓዣ ማዳበሪያ ሚዛን በጣቢያ በወረዳ እና በከተማ አስተዳደር በማደራጀት ለሕብረት ሥራ ማህበራት ማደራጃና ማስፋፊያ ጽ/ቤት ብድር ክትትል ክፍል በየሳምንቱ ሪፖርት ያቀርባል፡፡
6. በየምርት ዘመን መጨረሻ ከክልሉ ለሕብረት ሥራ ማህበራት ማደራጃና ማስፋፊያ ጽ/ቤት ጋራ በመቀናጀት የመጋዘን ኦዲት ያስደርጋል፡፡
7. ተጠቃሚዎች ለሚከፍሉት ገንዘብ የሚሰጥ ደረሰኝ ያዘጋጃል፡፡
8. የማዳበሪያ ሽያጭ ለማከናወንና ገንዘቡን ለባንክ በወቅቱ ገቢ ለማድረግ ውል ከግብርና ቢሮ ጋር ይዋዋላል፡፡
9. ከሽያጭ የተሰበሰበ ገንዘብ የአገልግሎት ክፍያ በመቀነስ በሶስት ቀናት ውስጥ በዘመኑ የማዳበሪያ ዕዳ ማስገቢያ የባንክ አካውንት ገቢ በማድረግ የባንክ ስሊፕ ኮፒ

10. Bushshu shiilo hirre gamba assinoonni womaashsha owaantete baatooshshe aaninni xeinse baanke eo assa hoongiro keeshshino barrubba womaashsha qallonte ledo shalangeenna baatate sooreessimma noosi,

11. Aganu aganunkunni bushshu shiilo hironna womaashsha qolli gara borrote ripoortenni giwirinnu biiroranna mittimmate loosi maamarra tantanonna halashsho borro minira shiqishanno.

12. Eotenna fulote shallago addinni qineessatenni hasi’nanni yannara odiiteretenni laisiissanno.

13. Woradu mittimmate loosi latishshi borro mininni uynanni hajajo garinni bushshu shiilo tuqinsoonni fulote darrasanyi halaalaanchimma buuxatenni kaimu mittimmate loosi maamarrara owaantete baatooshshe baatanno.

14. Kaimu mittimmate loosi maamarrara qajeelinoha shallagote loosaasinchonna woxu amadaancho gaamate gadadi noosi.

15. Hasiisiha ikkiro kilaasterete woy woradaho loosoho injo kalaqate umisi borro mini, biirote uduunni kompiyutere, kaaziinu, hattono xexxerrisu hee’ra hasiisanno.

16. Mittimmate loosi maamarrara woxu suuqonna liqoo, shallagote amadooshshinna womaashshu gashshooti aana dhuka kaajjishate looso loossanno.

17. Baatto loosidhe galtinori giwirinnu giwaate

ለወረዳ ኅብረት ሥራ ልማት ጽህፈት ቤት ያቀርባል፡፡

10. ከሽያጭ የተሰበሰበ ገንዘብ የአገልግሎት ክፍያ ተቀንሶ ባንክ ካልገባ ለቆየበት ቀናት ገንዘብን ከነወለዱ ተሰልቶ የመክፈል ኃላፊነት አለበት፡፡

11. በየወሩ የማዳበሪያ ሽያጭና የገንዘብ አመላለስ የጽሁፍ ሪፖርት ለግብርና ቢሮና ለሕብረት ሥራ ማህበራት ማደራጃና ማስፋፊያ ጽ/ቤት ያቀርባል፡፡

12. የገቢና ወጪ ሂሳቡን ለብቻ በማደራጀት በተፈለገ ጊዜ በኦዲተር ያስመረምራል፡፡

13. ከወረዳ የህብረት ስራ ልማት ጽህፈት ቤት በሚሰጠው ትዕዛዝ መሰረት ማዳበሪያ የተሰራጨበትን የወጪ ደረሰኝ ትክክለኛነቱን በማረጋገጥ ለመሰረታዊ ህብረት ሥራ ማህበራት የአገልግሎት ወጪ ይከፍላል፡፡

14. በየመሰረታዊ ህብረት ስራ ማህበሩ የሰለጠነ የሂሳብና ገንዘብ ያዥ ሠራተኛ የመቅጠር ግዴታ አለበት፡፡

15. እንደአስፈላጊነቱ በየክላስተሩ ወይም በየወረዳ ለስራው አመቺ የራሱ መስሪያ ጽህፈት፣ የቢሮ ቁሳቁስ ኮምፒዩተር፣ ካዝና እንዲሁም ሞተር ሳይክል ሊኖረው ይገባል፡፡

16. ለህብረት ስራ ማህበራት ስለ ገንዘብ ቁጠባና ብድር፣ ስለ ሂሳብ አያያዝና ገንዘብ አስተዳደር የአቅም ግንባታ ሥራ ይሰራል፡፡

hidhate ikkannonsaha suuqote budensa lossidhanno gede jawaachishate hayyo kalaqqe millissanno; jawaachishshanno.

## 16. Kaimu Mittimmate Loosi Maawarra

1. Woradu woy quchumu gashshooti aanno lekkishshi garinni lekkishsha uynoonninsa olluubbara ikkanno bushshu shiilo haa'ransa, agarate, tuqisatenna owaantete baatooshshe lainohunni woradu woy quchumu gashshmooti mittimate loosi borro mini ledo sheemaate e'anno.
2. Bushshu shiilo kuusate deerrasi agadhino kuusote mine qixxeessanno; shiqqanno bushshu shiilo bushshu shiilo owaantera calla attammoonni seerunniha ikkino darrasanyinni haadhe agarooshshe assanno; shiqanno darrasanyi garinni tuqisaanno.
3. Bushshu shiilo kuusote mini loosaasinchi kuusote mini gashshooti egenno noosiha ikkanno gede assanno; woy kuusote mini amadooshshi qajeelsha aanno.
4. Bushshsu shiilo kuuso mini sanyotenni kayse qidaamete geeshsha shoodihunni mitte saattenni kayse barrihunni tonaa lame saate geeshsha fano ikkite horoonsi'raanote owaante uytanno gede assinanni.
5. Haa'rino bushshu shiilo bikkinni sheemaatu simimmera xawinsoonni garinni shallange sasu

17. አርሶ አደሮች ለግብርና ግብዓት መግዣ የሚሆን የቁጠባ ባህል እንዲያዳብሩ የማበረታቻ ስልት ቀይሶ ይንቀሳቀሳል፣ ያበረታታል።

## 16. የመሠረታዊ ኅብረት ሥራ ማህበራት

1. በወረዳ ወይም በከተማ አስተዳደር በሚሰጠው ውክልና መሰረት ውክልና ለተሰጠባቸው ቀበሌያት የሚሆን ማዳበሪያ ስለመረከብ፣ ስለመጠበቅ፣ ስለስርጭትና የአገልግሎት ክፍያ አስመልክቶ ከወረዳ ወይም ከተማ አስተዳደር ኅብረት ሥራ ጽህፈት ቤት ጋር ውል ይገባል።
2. የአፈር ማዳበሪያ ለማከማቸት ደረጃውን የሚያሟላ መጋዘን ያዘጋጃል፣ የሚቀርብ ማዳበሪያን ለማዳበሪያ አገልግሎት ብቻ በታተመ ህጋዊ ደረሰኝ ተረክቦ ጥበቃ ያደርጋል፣ በሚቀርብ ደረሰኝ መሰረትም ያሰራጫል።
3. የአፈር ማዳበሪያ መጋዘን ሰራተኛ ስለ መጋዘን አስተዳደር እዉቀት ያለው ተቀጣሪ እንዲሆን ያደርጋል ወይንም ስለመጋዘን አያያዝ ስልጠና ይሰጣል።
4. የማዳበሪያ መጋዘን ከሰኞ እስከ ቅዳሜ ከጠዋቱ አንድ ሰዓት እስከ ቀኑ አስራ ሁለት ሰዓት ለተጠቃሚው ክፍት ሆኖ አገልግሎት እንዲሰጥ ያደርጋል።
5. በተረከበው ማዳበሪያ መጠን በውል ስምምነቱ በተገለፀው መሠረት ተሰልቶ በየሦስት ወሩ ወይም እንደ አስፈላጊነቱ

aganinni, hasiisiha ikkiro ajjino yannanni mittimmate loosi borro mini hajajanno gede assine owaantete baatooshshe adhitanno.

6. Baatto loosidhe galtinori bushshu shiilo hidhate daganno woyte olluunnihu qaru gashshaanchi, olluunnihu giwirinnu borro mini sooreessinna loosu ha’risaanchi mitteenni sokkino malaati garinni jeefinsanni.

7. Beenkoonniha bushshu shiilo buuxate loosidhe galtinori su’ma, darrasanyanna bushshu shiilo bikka hattono gatinoha bushshu shiilo amaddino taje lamala lamalatenni woradu mittimmate loosi borro minira shiqishanno.

8. Bushshu shiilo haa’nanni woyte waagunni shalange birru bikkinni mittimmate loosi maamari su’minni amandanni bushshu shiilo taje lamala lamalatenni woradu mittimmate loosi borro miniranna maamaraho shiqishe xaadisi’ranno.

## GAFA SHOOLE

## Bushshu Shiilo Shiqo, Tuqishshanna Womaashshu Gashshoote Massagganno Qineessote Komite

### 17. Uurrisa

Hundaanchimmasi deerru deerrukunni heedhanno gashshoottira woy gashshootu amaale minira ikkinohu bushshu shiilo shiqo, tuqishshanna womaashshu gashshooti amanyoote harunsitannonna

ባነሰ ጊዜ ከህብረት ስራ ጽህፈት ቤት እንዲታዘዝ በማድረግ የአገልግሎት ክፍያ ይቀበላል፡፡

6. አርሶ አደሩ ማዳበሪያ ለመግዛት ስመጣ የቀበሌው ሊቀመንበር፣ የቀበሌው ግብርና ጽ/ቤት ኃላፊና ስራ አስኪያጅ በጣምራ በላኩት ፊርማ መሰረት ይፈጸማል፡፡

7. የተሰራጨ የአፈር ማዳበሪያ ለማገናዘብ የአርሶ አደሮችን ስም ዝርዝር፣ ደረሰኝ እና የማዳበሪያ መጠን እንዲሁም የቀሪ ማዳበሪያ ሚዛን የያዘ መረጃ በየሣምንቱ ለወረዳው ኅብረት ሥራ ጽህፈት ቤት ያቀርባል፡፡

8. የአፈር ማዳበሪያ ስረከቡ በዋጋ ተሰልቶ በገንዘብ መጠን በህብረት ስራ ማህበሩ ስም ስለሚያዝ የማዳበሪያ ሚዛን የያዘ መረጃ በየሣምንቱ ለወረዳው ኅብረት ሥራ ጽህፈት ቤትና ለማህበሩ አቅርቦ ይናበባል፡፡

## ክፍል አራት

## የአፈር ማዳበሪያ አቅርቦት፣ ስርጭትና ገንዘብ አስተዳደር የሚመራ አስተባባሪ ኮሚቴ

### 17. መቋቋም

ተጠሪነቱ በየደረጃው ለሚገኝ አስተዳደር ወይም ለአስተዳደር ምክር ቤት የሆነ የአፈር ማዳበሪያ አቅርቦት፣ ስርጭት፣ የገንዘብ አስተዳደር ስርዓት የሚከታተልና የሚመራ አስተባባሪ ኮሚቴ ከዚህ በኋላ “አስተባባሪ

massagganno qineessote komite konni gedenoonni "Qineessote Komite" yine woshshinanniti qoqqowunni kayse olluu geeshsha tenne wodhonni uurrinsoonni.

**18. Qoqqowu Qineessote Komite**

1. Giwirinnu biiro sooreessi …….. gambisaancho
2. Giwirinnu giwaate shiqonna baadiyyete faynaansete handaari sooreessi ………. laynki gambisaancho
3. Mittimmate loosi maamarra tantanonna halashsho borro mine sooreessi …….. borreessaancho
4. Qoqqowu faynaansete biiro sooreessi …….. miila
5. Qoqqowu mittimmate loosi giwaatenenna laalchu dikki'rate dayrekiteroote dayrekitere ……… miila
6. Sidaamu Elto yuneene loosu ha'risaanchi ………. miila
7. Itiyophiyu daddalu baanke Hawaasi disitirkite loosu ha'risaanchi ………….. miila
8. Qoqqowu pirezidaantichi miinju hajo amaalaanchi ………………. miilla
9. Qoqqowu poolisete komishiine komishiinerchi ………… miila

ኮሚቴ" እየተባለ የሚጠራ ከክልል እስከ ቀበሌ በዚህ ደንብ ተቋቁሟል፡፡

**18. የክልል አስተባባሪ ኮሚቴ**

1. የግብርና ቢሮ ኃላፊ …………… ሰብሳቢ
2. የግብርና ግብዓት አቅርቦትና ገጠር ፋይናንስ ዘርፍ ኃላፊ …….. ምክትል ሰብሳቢ
3. የሕብረት ሥራ ማህበራት ማደራጃና ማስፋፊያ ጽ/ቤት ኃላፊ ………. ፀሐፊ
4. የክልሉ ፋይናንስ ቢሮ ኃላፊ ……… አባል
5. የክልሉ የህብረት ሥራ ግብዓትና ምርት ግብይት ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር ……….. አባል
6. የሲዳማ ኤልቶ ኅብረት ሥራ ዩኒየን ሥራ አስኪያጅ ………. አባል
7. የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ሀዋሳ ዲስትሪክት ስራ አስኪያጅ …………. አባል
8. የክልሉ የርዕሰ መስተዳድር የኢኮኖሚ አማካሪ ……….. አባል
9. የክልሉ ፖሊስ ኮሚሽን ኮሚሽነር ………… አባል

**19. Woradu Woy Quchumu Gashshooti Qineessote Komite**

1. Woradu woy quchumu gashshooti giwirinnu borro mini soorreessi …………. gambisaancho
2. Woradu woy quchumu gashshooti mittimmate loosi maamarra tantanonna halashsho borro mine sooreessi ……………. laynki gambisaancho
3. Woradu woy quchumu gashshooti mittimate loosi giwaatetenna laalchu dikki'rate gaamo massagaanchi ………………. borreessaancho
4. Woradu woy quchumu gashshooti faynaansete borro mini sooreessi ………….. miila
5. Woradu woy quchumu gashshooti poolisete hajajaanchi ………….. miila
6. Woradu woy quchumu gashshooti giwirinnu giwaatenna baadiyyete faynaanse gaamo massagaanchi …………. miila
7. Woradu woy quchumu gashshooti giddo heedhanno Itiyophiyu daddalu baanke loosu ha'risaanchi …………… miila

**20. Olluu Qineessote Komite**

1. Olluu gashshaanchi …………. Gambisaancho
2. Ollu giwirinnu borro mini sooreessi …………….. borreessaancho
3. Olluu loosu ha'risaanchi ……………. miila
4. Mittimmate loosi tantano massagaanchi

**19. የወረዳ ወይም ከተማ አስተዳደር አስተባባሪ ኮሚቴ**

1. የወረዳ ወይም ከተማ አስተዳደር ግብርና ጽህፈት ቤት ኃላፊ ………… ሰብሳቢ
2. የወረዳ ወይም ከተማ አስተዳደር የሕብረት ሥራ ማህበራት ማደራጃና ማስፋፊያ ጽ/ቤት ኃላፊ ………… ምክትል ሰብሳቢ
3. የወረዳ ወይም ከተማ አስተዳደር የህብረት ሥራ ግብዓትና ምርት ግብይት ቡድን መሪ ……………. ፀሐፊ
4. የወረዳ ወይም ከተማ አስተዳደር ፋይናንስ ኃላፊ ……………. አባል
5. የወረዳ ወይም ከተማ አስተዳደር ፖሊስ አዛዥ ………… አባል
6. የወረዳ ወይም ከተማ አስተዳደር ግብርና ግብዓትና ገጠር ፋይናንስ ቡድን መሪ …………. አባል
7. በወረዳው ወይም ከተማ አስተዳደር የሚገኝ የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ቅርንጫፍ ስራ አስኪያጅ ………………. አባል

**20. የቀበሌ አስተባባሪ ኮሚቴ**

1. የቀበሌ አስተዳዳሪ ………… ሰብሳቢ
2. የቀበሌ ግብርና ጽህፈት ቤት ኃላፊ .... ፀሐፊ
3. የቀበሌ ሥራ አስኪያጅ ………… አባል
4. የህብረት ሥራ አደራጅ ባለሙያ ባለበት

……………. miila

5. Bushshu shiilo tuqisanno kaimu mittimmate loosi maamari murrichi ………….. miila

**21. Qineessote Komite Loosonna Sooreessimma**

1. Tenne wodho garrinni uurritino qineessote komite bushshu shiilo shiqo, tuqishshanna womaashshu gashshooti looso aliidimmatenni harunsitanno; massagganno; irkissanno.
2. Jeefishshu ripoorte deerru deerrunkunni hee'ranno gashshootu amaale minira aganu aganunni shiqishanno.
3. Bushshu shiilo womaashshi liqiissitino baankera iillasi buuxxanno.
4. Bushshu shiilo shiqo, tuqishshinna womaashshu gashshooti loosi jeefishsha harunsitanno; xaaddanno qarrubba badatenni tirote hedo shiqishshanno.

**22. Komitete Gambooshshi Yannanna Gumulo Aate Amanyoote**

1. Komitennihu uurrinshu gambooshshi aganunni mitte hige iikkanna hasiisiha ikkiro wiinamu gambooshsheno gambisaanchu woy laynki gambisaanchi widoonni woshshinara dandiinanni.
2. Komitete miilla mereerinni lamunni sayikki anga leelturo songo guuta ikkitanno.

……… አባል

5. የአፈር ማዳበሪያ አሰራጭ መሰረታዊ ኅብረት ስራ ማኅበር ሊቀመንበር … አባል

**21. የአስተባባሪ ኮሚቴ የወል ኃላፊነትና ተግባር**

1. በዚህ ደንብ መሰረት የተቋቋሙ አስተባባሪ ኮሚቴዎች የአፈር ማዳበሪያ አቅርቦት፣ ስርጭት፣ የገንዘብ አስተዳደር ተግባርን በበላይነት ይከታተላል፤ ይመራል፣ ይደግፋል፡፡
2. የአፈጻጸም ሪፖርት በየደረጃው ለሚገኝ አስተዳደር ምክር ቤት ሪፖርት በየወሩ ያቀርባል፡፡
3. የአፈር ማዳበሪያ ገንዘብ ለአበዳሪ ባንክ መድረሱን ያረጋግጣል፡፡
4. የአፈር ማዳበሪያ አቅርቦት፣ ስርጭት፣ የገንዘብ አስተዳደር ተግባር አፈጻጸምን ይከታተለል፣ የሚያጋጥሙ ችግሮችን በመለየት የመፍትሔ ሀሳብ ያቀርባል፡፡

**22. የኮሚቴው የስብሰባ ጊዜና የውሳኔ አሰጣጥ ሥነ-ሥርዓት**

1. የኮሚቴው የመደበኛ ስብሰባ ጊዜ በወር አንድ ጊዜ ሆኖ እንደአስፈላጊነቱ አስቸኳይ ስብሰባዎችን በሰብሳቢው ወይም ምክትል ሰብሳቢው አማካይነት ሊጠራ ይችላል፡፡
2. ከኮሚቴው አባላት መካከል ሁለት ሶስተኛው በስብሰባው ላይ ከተገኙ ምልዓተ-ጉባኤ ይሆናል፡፡

3. Komitete gumulo rooriidi huuronni kaajjitanno. Ikkollana huuro taalo ikkituro gambisaanchu irkisanno gumulote hedo jeefishsha afidhanno.

**GAFA ONTE**

**<u>Addi Addi Woro</u>**

**23. Halamate Gadacho**

Aye manchino tini wodho wo’mu garinni loosu aana hossanno gede hasiissanno irko aatenna halamate gadacho noosi.

**24. Xa’mamooshshe**

Tenne wodhonni hanqafantino hajubba jeefishsha gufusannohu hunaanchimmasi bikkinni gashshootu qaafo, fitaabeerete hattono jaddote seerinni xa’mamannoha ikkanno.

**25. Jeefishshu Nookki Seerinna Assooti**

1. Sidaamu dagoomu qoqqowi mootimma rosamino mootimmate loosira albi qoqqowinni fultino wodhubba loosu aana hosansa sufantanno gede fajjate fultino wodho kiiro 6/2013 quwa 3 garinni fajjinoonni albi qoqqowi bushshu shiilo shiqishonna iillisho wodho kiiro 124/2007 tenne wodhonni shaaroonni.

2. Tenne wodhonni kiphantannoti ayee wodho, biddissi woy rosamino assooti tenne wodhonni hanqafantino hajubba la”annohunni jeefishshu dihee’rannonsa.

3. የኮሚቴው ውሣኔ በድምጽ ብልጫ ይፀድቃል፡፡ ሆኖም ድምጹ እኩል ከሆነ ሰብሳቢው የሚደግፈው የውሳኔ ሀሳብ ተፈጻሚነት ይኖረዋል፡፡

**ክፍል አምስት**

**<u>ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች</u>**

**23. የመተባበር ግዴታ**

ማናቸውም ሰው ደንቡ በተሟላ መልኩ እንዲተገበር አስፈላጊውን ድጋፍ የመስጠትና የመተባበር ግዴታ አለበት፡፡

**24. ተጠያቂነት**

በዚህ ደንብ የተሸፈኑ ጉዳዮች ተፈጻሚነት እንዲጓደል የሚያደርግ እንደጥፋቱ መጠን በአስተዳደራዊ እርምጃ፣ በፍትሐ ብሔር እንዲሁም በወንጀል ሕግ ተጠያቂ ይሆናል፡፡

**25. ተፈጻሚነት የሌላው ሕግና አሰራር**

1. በሲዳማ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ለመደበኛ መንግስታዊ ሥራዎች በነባሩ ክልል የወጡ ደንቦች ተፈጻሚነት እንዲቀጥል ለመፍቀድ በወጣ ደንብ ቁጥር ፮/፳፻፲፫ አንቀጽ ፫ መሠረት የተፈቀደው የነባሩ ክልል የአፈር ማዳበሪያ አቅርቦትና ስርጭት ደንብ ቁጥር ፻፳፬/፳፻፯ በዚህ ደንብ ተሽሯል፡፡

2. ይህንን ደንብ የሚቃረን ማንኛውም ደንብ፣ መመሪያ ወይም ልማዳዊ አሰራር በዚህ ደንብ ለተሸፈኑ ጉዳዮች ተፈጻሚነት

**26. Biddissa Fushshate Biilloonye**

Tenne wodho tittrishunni loosu iima hosiisate hasiissanno biddissa biiro fushshate dandiitanno.

**27. Wodho Loosu iima Hossanno Yanna**

Tini wodho Badheessa 1/2013 M.D hanaffe loosu iima hossanno.

**Hawaasa, Badheessa 10, 2013 M.D**

**Desta Ledamo**

**Sidaamu Dagoomu Qoqqowi Mootimma Pirezidaanticha**

የላቸውም፡፡

**26. መመሪያ የማውጣት ሥልጣን**

ይህን ደንብ በዝርዝር ሥራ ላይ ለማዋል የሚያስፈልግ መመሪያ ቢሮው ሊያወጡ ይችላሉ፡፡

**27. ደንቡ ሥራ ላይ የሚውልበት ጊዜ**

ይህ ደንብ ከመጋቢት ፩ ቀን ፳፻፲፫ ዓ.ም ጀምሮ በሥራ ላይ ይውላል፡፡

**ሀዋሳ፣ መጋቢት ፲ ቀን ፳፻፲፫ ዓ.ም**

**ደስታ ለዳሞ**

**የሲዳማ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት**

**ርዕሰ መስተዳድር**